የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ		
I አጠቃላይ መግለጫ		
የመስሪያ ቤቱ ስም በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር	የሥራ መደቡ መጠሪያ የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ደረጃ 4 አካባቢ ጤና አጠባበቅ ቴክኒሽያን II	የህብረተሰብ ጤና
	በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር.ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ/ተጠሪነት	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
ቡድን መሪ	X	
መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
ጤና ጣቢያ / ሆስፒታል / ማዘጋጃ ቤት		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

2..1 የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- የህፃጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ በጤና ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ የመከላከልና የማላመድ ተግባራትን በመተግበር፣ አካባቢያዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር እና የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመስራት ህብረተሰቡን ከተላላፊ በሽታዎች መጠበቅ እና ከብክለት የፀዳ ምቹ አካባቢ መፍጠር ነው።

2..2 ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፣ ለአካባቢ ጤና አገልግሎት የሚውሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማጠናቀር

- የመረጃ ማሰባሰቢያ፣ ማደራጃና ማጠናቀሪያ ቅፆችንና ቼክሊስቶችን ለማዘጋጀት የሚረዱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፣
- የህፃጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥና ጤናን አስመልክቶ በግለሰብ፣በማህበረሰብ፣በተቋማትና በድርጅቶች ደረጃ አካባቢያዊ መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣
- ድንገተኛ አደጋዎችና ወረርሽኞችን ለመከላከልና ለመቆጣጣር ዙሪያ መረጃ ይሰበስባለል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል
- የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሻሻል የጤና መልዕክቶች ዝግጅት የሚረዳ መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣
- የሥራ ክለፍሉን ጠቋሚ፣ አንኳርና ዝርዝር ዕቅድ የሚረዱ መረጃዎችን ይሰበስባ ያዘጋጃል፤
- የሥራ መረጃ እና ዕቅድ አፈፃፀም መረጃ ይሰበስባል፣ ሪፖርቶች ያዘጋጃል፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል

ውጤት፤**2** የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን በመተግበር ማህበረሰቡን ከተላላፊ በሽታዎች መጠበቅ_

- የተለያዩ የመጸዳጃ ቤቶች አሰራር፣አያያዝና አጠባበቅ አስመልክቶ ለማህበረሰቡ ትምህርት በመስጠትና በተመረጡ ማህበረሰቦች/ቦታዎች ሰርቶ ማሳያዎችን በመስራት በቀላሉ እንዲተገበሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፡
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘዴዎችን በተመለከተ ለማህበረሰቡ የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ በተግባር እንዲተረጎሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
- የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘዴዎችን በተመለከተ ለማህበረሰቡ የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ በተግባር እንዲተረጎሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
- በአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉደለት የተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን ለህብረተሰቡ ያሳውቃል፣የተነደፉ የመቆጣጠሪያ ስልቶችን እንዲተገበሩ ያደርጋል።
- በአከባቢ ጤና አጠባበቅ ጉደለት ተላላፊ በሽታዎች ሲከሰቱ ለሚመለከተዉ ሪፖርት ያደረጋል፤
- በተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ አደጋ ወቅት ከሌሎች መሰል ጤና ባለሙያዎች ጋር በመሆን አስፈላጊው የህፃጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን ተግባራዊ በማድረግ በሽታዉ እንዳይከሰት/ እንዳይሰራጭ የመከላከል ሥራ ይሰራል ።
- የከባቢና የቤት ውስጥ አየር ብክለት በጤና ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመከላከል ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለማህበረሰቡና ሊሎች ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ በተግባር እንዲተረጎሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል።